የሰ/መ/ቁ. 20036

ግንቦት 16 ቀን 1998

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሠ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
· ምህረቱ
መዐዑ ን እቁበዮናስ
ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች:- ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ተጠሪ:- ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሊከፈል የማይገባው የጡረታ አበል ክፍያን የሚመለከት ነው::

አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ተጠሪ የሟች ባለቤታቸውን የወ/ር ተፈራ አድማሱን ጡረታ እየተቀበሉ ሌላ ባል በማግባታቸውና፤ የሟች ባላቸውን ጡረታ አበል እየበሉ ሌላ ባል ያገቡ የጡረታ አበል እንደሚቋረጥባቸው ሕጉ ግልፅ ሆኖ ሣለ፤ ይህንኑ በመቃረን



ተጠሪ ሌላ ባል አግብተውም የሟችን ጡረታ ለ 13 አመታት ስለተቀበሉ በድምሩ ብር 7593.75 ይክፈሉ በማለት ጠይቋል::

ተጠሪም ቀርበው ከ13 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ሌላ ባል አላገባሁም ከጋብቻ ውጪ በነበረን ግንኙነት 2 ልጆች ወልጃለሁ በማለት ተከራክረዋል::

ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ክስ የቀረበበት የይመለስልኝ ጥያቄ በየጊዜው (በየወሩ) የሚከፈልና ለመጨረሻም ጊዜ ክፍያው የተደረገው በ ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ሲሆን ክስ የተመሠረተው በሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ አላለፈም፣ ነገር ግን ተጠሪ ሌላ ባል ያገቡ ለመሆናቸው አላስረዳም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል::

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ውሣኔ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል::

የአሁኑ አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው:: ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ መሃከል ጋብቻ መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር አ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል::

አመልካች ክስ የመሠረተው መክፈል የማይገባኝን የጡረታ አበል የከፈልኩ ስለሆነ ይመለስልኝ በሚል ነው:: ይህ ደግሞ በፍ/ብሔር ሕጉ ያለአግባብ ስለመበልፀግ ከሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የማይገባውን ስለመካፈል በሚለው ክፍል ሥር የሚወድቅ ነው:: አንድ ሠው ሊከፍል የማይገባውን ነገር ከከፈለ እንዲመልስለት የመጠየቅ መብት እንዳለው የፍ/ህ/ቁ 2164 (1) ያመለክታል::

በተያዘው ጉዳይ በጡረታ ሕጉ በባልዋ መሞት ምክንያት ጡረታ የምታገኝ ሴት ሌላ ባል ባገባች ጊዜ የሟች ባሏ ጡረታ አበል መቋረጥ ያለበት ለመሆኑ ተመልክቷል:: የተጠሪ የመጀመሪያ ክርክር ክስ የቀረበበት ጉዳይ 10 አመት ስላለፈው በ10 አመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው::

የማይገባውን ስለ መክፈል የሚለው ክፍል የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሃላፊነትና ያላግባብ ስለመበልፀግ በሚናገረው አንቀፅ ሥር ነው:: በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በዚሁ አንቀፅ ተካቶ የሚገኘው የይርጋ ጊዜ

ይሆናል:: የፍ/ህ/ቁ 2143(1) ተበዳይ ክስ ማቅረብ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሠ ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ነው:: አመልካች መክፈል የማይገባውን ነገር መክፈል የጀመረው ከህዳር ከህዳር 1 ቀን 1981 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ክፍያ ያቋረጠው ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ነው:: በመሆኑም አመልካች ክስ ከቀረበበት ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ወደኋላ ያለው የሁለት አመት ጊዜ ብቻ በይርጋ ቀሪ የማይሆን ሲሆን ከዚህ ጊዜ በፊት የነበረው የአመልካች ጥያቄ ግን በይርጋ ቀሪ ይሆናል::

ሌላው የተጠሪ ክርክር ከአቶ ገብሩ አሰፋ ጋር ጋብቻ የለንም:: ከጋብቻ ውጪ ባለ ግንኙነት ነው ልጆች የወለድኩት የሚል ነው::

ከፍ/ቤቱ መዝገብ ተጠሪ አቶ ገብሩ አሰፋ ባላቸው መሆናቸውን በቀበሌ ቅፅ ላይ ሞልተው አረጋግጠዋል:: አቶ ገብሩ አሠፋም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ላይ ተጠሪ ሚስታቸው መሆናቸውን አረጋግጠዋል:: ከዚህም በላይ ተጠሪ ከጋብቻ ውጪ ነው ይበሉ እንጂ እንደ ባልና ሚስት በመሆን አንድ ላይ ይ በር አልካዱም::



በተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ 5 ላይ ጋብቻ መኖሩን ለማረጋገጥ ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ማስረጃ በሌላ ጊዜ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 95 እንደተመለከተው የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ጋብቻን ማስረዳት ይቻላል:: የትዳር ሁኔታ አለ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ እንዲሁም ማሕበረሰቡና ቤተዘመዶቻቸው እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው ተብሎ በአንቀጽ 96 ስር ተጠቅሷል ፡፡ ይህን ሁኔታ ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድም አንቀጽ 97 ያመለክታል። ሕጉ የጋብቻ ሁኔታ የሚረጋገጥበትን ማስረጃ አይነት ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑም ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል::

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪና በአቶ ገብሩ አሰፋ መሃከል ጋብቻ መኖሩን የጋብቻ (የትዳር) ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት ማስረጃዎቹን አቅርቧል:: ተጠሪ አቶ ገብሩ ባላቸው ለመሆናቸው በቀበሌ ፎርም ላይ ሞልተው ማረጋገጣቸውን እንዲሁም አቶ ገብሩም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ተጠሪዋ ሚስታቸው መሆናቸውን አረጋግጠው መሙላታቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል:: ይህም ተጠሪና አቶ ገብሩ እራሣቸውን እንደባልና ሚስት እየቆጠሩ የሚኖሩ መሆኑን ማህበረሰቡም በዚሁ መልኩ የተቀበላቸው መሆኑን ያመለክታል:: ነገር ግን የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የአቶ ገብሩ ሚስት ለመሆናቸው የጋብቻ ሠርተፍኬት አልቀረበም ወይም ሠርተፊኬቱ መጥፋቱ አልተረጋገጠም በማለት በሁለቱ መሃከል ትዳር የለም በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የቤተሠብ ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው::

ዐ



1. ተጠሪ ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም 0 ቀን 1995 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የወሰዱትን የሟች ባለቤታቸውን የጡረታ አበል ለአመልካች ይመልሱ::
2. ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም በፊት አመልካች ለተጠሪ የከፈለው የጡረታ አበል እንዲመለስ ያቀረበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል::
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ:: መዝገቡ ተዘግቷል:: ለመ/ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።